# በተወዳጁ ሰሎሞን ሃድጎ ንጉሤ (ጋንፉር) ዜና ዕረፍት የቀበና አብሮ አደጎቹ የተሰማቸው ጥልቅ ሃዘን መግለጫ

በሰው ወዳድነቱ፤ አክባሪነቱ፤ በቅን አስተሳሰቡ፣ በፍልቅልነቱ፣ በትሁትነቱ፣ በማህበራዊ ዝግጅቶች አስተባባሪነቱ፣ ከሁሉም በላይ በርህሩህ ሰብዕናው ለተገፉ፤ በድህነት ለሚማቅቁና ፍትህ ላጡ ወገኖች በመቆም የሚታወቀው የሰሎሞን ጋንፉር በድንገት ከዚህ ዓለም በሞት መለየት የቀበና አብሮ አደጎቹን አስደንግጦናል፤ ከፍተኛ የሃዘን ድባብ ውስጥ ከትቶናል።

ጋንፉር ተወልዶ ባደገበት ቀበና ኮርያ ሰፈር 'የሕዝብ ልጅ' በመባል ነበር የሚታወቀው። በአዛውንቱ፤ በወጣቱም ሆነ በሕጻናቱ ሕይወትና ልብ ውስጥ ጋንፉር ማለት ደስታ ማለት ነበር። እርሱ ያለበት፣ እርሱ የገባበት ማንኛውም ማህበራዊ ዝግጅትና ስብስብ ሁሉ ይሞቃል፤ ይደምቃል። ደስታንና መዝናናትን በሰዎች አእምሮ ውስጥ የመናኘት ልዩ ተሰጥዖ ነበረው። በልጅነታችን የአካባቢው ወጣቶች 'ቃኘው በኮሪያ' በሚል ስያሜ አቋቁመውት በነበረው ማህበር ውስጥ የጋንፉሬ አስተዋጽኦ ጉልህ ነበር።  በማህበሩ የመዝናኛ ዝግቶች ላይ ጋንፉሬ ያላጀበው ዘፈንም ሆነ ድራማ ድምቀት አይኖረውም ነበር።

የተወሰኑ ከአገር ውጪ የሚኖሩ የቀበና አካባቢ አብሮ አደጎች ለመሰባሰብ፤ ለመጠያየቅ ብንሞክርስ ብለው ሲነሱ ዋናው ደጋፊና ጉዳዩን ከሃሳብ ወደተግባር እንዲሸጋገር ከገፉፉት ውስጥ ጋንፉሬ ዋነኛው ነበር። የመጀመሪያው የአብሮ አደጎች የመሰባሰቢያ ቀን ሰኔ 1 ቀን 2006 (ጁላይ 6 ቀን 2013) ሲዘጋጅ ጋንፉር መላውን የቤተሰብ አባላቱን አሰማርቶ፤ ገንዘብ ንብረቱን ሁሉ አፍስሶ የደመቀ ዕለት እንዲሆን አደረገ። ዝግጅቱን በዋና አዘጋጅነት መራ፤ አስተባበረ። ራቅ ካሉ ሥፍራዎች ለዝግጅቱ የመጡትን በቤቱ ተቀብሎ አስተናገደ። ያለፉት ሁለት ተከታታይ ዓመታት ዝግጅቶችንም እንዲሁ የሞቁ፤ የደመቁና የተሳኩ እንዲሆኑ አደረገ።

ጋንፉር፤ የቀበና አብሮ አደጎች የመሰባሰብ ሂደት ማዕከል ነበር፤ ድንኳናችን ነበር። በእያንዳንዳችን የግልም ሆነ ማህበራዊ ህይወት ውስጥ በጎ የሆነ አሻራና ልዩ ስፍራ ነበረው። ጋንፉሬ ባለፈው ወር የመጨረሻ እሁድ ላይ ያካሄድነውን የስልክ ስብሰባ መርቶ፤ ቀጣይ ስብሰባችንን ለጃንዋር 3 ቀን ቀጥሮ ነበር የተለያየነው። ከሁለት ዓመታት በፊት በደረሰበት ህመም ካስከተለብን ድንጋጤ ሳንወጣ፤ ከዚያ ወዲህ ሁሌም እንደሳሳንለት ይህ ድንገተኛ አደጋ ተከሰተ። አሰባሳቢያችን፤ የተስፋችን ምንጭ፤ የቀበና የቀድሞ ህይወታችን መዘክር ለመጨረሻው ተለየን።

በቀበና አብሮ አደጎች ስም ጥልቅ ሀዘናችንን እየገለፅን፤ ለውድ ባለቤቱ ለወይዘሮ ኤልሳቤጥና ለልጆቻቸው፣ እንዲሁም ለእህቶቹ፣ ለመላ በሩቅም በቅርብም ላሉ ዘመዶቹና በተለያየ የህይወት ጉዞው ላፈራቸው ወዳጆቹ ሁሉ መጽናናት እንዲሰጣቸው እንመኛለን።

የቀበና አብሮ አደጎች አሰባሳቢ

ታህሳስ 14 ቀን 2008 (24 December 20015)



**ጋንፉሬ፤ ሁሌም በልባችን ትኖራለህ**

## እሪ በይ ቀበና

እሪ በይ ቀበና፤ እሪ በይ ሰፈሬ፤  ዛሬም እንደገና
ሌላውን ብርቅዬ ፤ ሌላውን ተሚጋች ሸኝተሻልና።
ካንድም ሁለት ሦስቴ የተፈተነልሽ
ሁሉንም ድል አርጎ አፋፍ ብቅ ያለልሽ
ያ ደፋሩ ልጅሽ፣ ጋንፉሬ ወዳጅሽ፣ ጋንፉሬ አከባሪሽ
የሆዱን በሆዱ፣ የልቡን በልቡ፣ እንደቋጠረልሽ
ቻው እንኳን ሳይልሽ፤ ሳይሰናበትሽ።
ቀድመው የሄዱትን ፤ ጥንት የተሸኙትን
ካንቺ የራቁትን፤ እናቱን፣ አባቱን፣ ወንድሙን፣ ጓዶቹን
ሊጠይቅ ሊጎበኝ ናፍቆቱን ሊናገር
ከማንም ሳይመክር፤ ለማንም ሳይነግር
ሄደልሽ፤ ራቀልሽ፤  ምሎ ተገዝቶ ድጋሚ ላያይሽ
ጸጥ እረጭ አለልሽ፤ ያ ታጋዩ ልጅሽ
እሪ በይ ቀበና ፤ አልቅሺ ቀበና ፤ ዛሬም እንደገና
ድል አድራጊው ጀግና፣ ድል አድራጊው ልጅሽ፣
እጁን  ሰጥቷልና።

**ቆለኛው**
(ከቀበና ኮርያ ሰፈር)

## ቆይ ባክህ፤ ጋንፉሬ

ቆይ ባክህ ጋንፉር
ሰብሳቢያችን አባት ነገር
ባክህ አንዴ እንነጋገር?
በረሃብ፤ በጥም በቁር
በጥይት፤ በቦምብ በሃሩር
በገደሎች ዝቅታ
በተራሮች ከፍታ
ያልተናጋ ያልተረታ
እንዴት ተሰፋህ፤ በሞቀ ከተማ ተፈታ?
ይህ ግለኝነት፤ ከየት መጣ ከወደኋላ?
ለአገር፤ ለህዝብ መሞት አልነበረም
የአንተ ትውልድ መሃላ?
አንተ ከሞትህማ
ያፍሩሱት ያን ከተማ
ቀበና ኮሪያ ሰፈር፤ እትብትህ የረፈበትን አውድማ።
ሰብሳቢያችን፤ እባክህ ቆይ
አንድ ቀን እንኳን እንጫወት ቀበና ላይ።

**ደገኛው**
(ከቀበና)